# ሰዶ ማሳደድ ያማረው ዶሮን በቆቅ ይለውጣል!

ከአቶ ሰውየው

ባለፈው ወር፣ በየፓልቶክ መድረኩ (ለምሳሌ ከረንት አፌር - ዴሞን በዲሞት ፎር እያለች በቀይ ሽብሩ ወቅት የደርግ የነጻ እርምጃ ቀስቃሽና ለፍርድ ልትቀርብ የሚገባት አዛውንት ማለትም ሙያዬ ምሥክርና ሌሎችም) አማካይነት፤ የተለያዩ ራዲዮና ድህረ-ገጾችና የመሳሰሉት የመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት በኢሕአፓ ለይ የተነጣጠረ ልዩ ዘመቻ ተከፍቷል። ለዚህ ወገራ በድንጋይ አቀባይነት በሰፊው የተሰማሩት ደግሞ በሚያሳዝን ሁናቴ አሕአፓ ነበርን (ነን) የሚሉን ወገኖች ራሳቸውን የእርማት እንቅስቃሴ፣ ትንሳኤ ኢሕአፓና ያው ከጥቂት ዓመታት በፊት ድርጅቱን ጥለው የወጡ ኢሕአፓ ዴ ነን የሚሉን ወገኖች ሆነው መገኘታቸው በጣም አሳዝኖኛል። በየድረ-ገጹ የተበተኑትን ሁለት በራሪ ወረቀቶችና ሁለት በቀጥታ የኢሕአፓን መሪ ኢያሱ ዓለማየሁን የሚያጣጥሉ ጽሑፎች፣ አንደኛው ኢያሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፉ በአማርኛ በአዲስ አበባ መተርጎምና በዋቢ ሸበሌ መመረቅ አስመልክቶ ኢያሱ ከወያኔዎች ጋር እየሠራ ነው ዓይነት ክስ የሚያቀርብ ሌላው ደግሞ በእንግሊዝኛ በኢድን የኢሜል ሊስትና በተለያዩ አቅጣጫዎች የተበተነውን የእንግሊዝኛ  መጣጥፍ እነሆ ከዚህ ጽሑፍ ግርጌ አባሪ አድርጌ ባቀርብኳቸው ላይ የግል አስተያየቴን እነሆ አቀርባለሁ።

በበኩሌ ኢሕአፓን እናጠናክር የሚሉን ወገኖች የሚከተሉት ሂደት በእርግጥ የማጠናከር ወይስ የማጥቃትና የማጥላላት ዘመቻ ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘትና አቋም መያዝ ለድርጅቱ ከፍተኛ አክብሮት ላለን የድርጅቱ ደጋፊዎች ነን ለምንል ሁሉ ተወደደም ተጠላ ጊዜው የሚጠይቀው ግዳጃችን ነው።  በሁለት ቢላ መብላት አይቻልም። በተለይም ከላይ እንደምሳሌ የጠቀስኳቸው ዓይነት መጣጥፎች የሚሰዱብን ወገኖች የሚፈልጉት ምንድር ነው? የውሸት ጋጋታውንስ ምን አመጣው? ለምሳሌ አቶ ኢያሱ ከሻዕቢያው መሪ ከአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ተስማምቶ ሳተላይት ራዲዮ ሊያቋቁም ነው በሚለው ሊረጋገጥ የማይቻል ወሬ በእንግሊዝኛ የተለቀቀው ወረቀት ውስጥ ሌላው ውሸት ደግሞ አቶ የማነ አብ ገብረ አብ (አዲስ አበባን የማያውቅ ሰው) በምንም ዓይነት ከአቶ ኢያሱ ጋር ትምህርት ቤት አብረው ሊማሩ እንደማይችሉ እየታወቀ ይሄን የዳበረ ውሸት ሳያፍሩ የሚሰዱብን ሰዎች ዓላማ ምንድር ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ከፊታችን ግልጽ ሆኖ እናገኛዋለን። ለኔ ግልጽ ነው። አፍራሽነት! ማንአኸሎኝነት! ደካማነት! እና ንቀትም ጭምር ነው። ገና ለገና የፍኖተ-ዴሞክራሲ ራዲዮ ጣቢያን የማጠናከር ፍንጭ በድርጅቱ ደጋፊዎች አካባቢ ታየ ተብሎ አስቀድሞ የማሽመድመድ ዘመቻ! ጉድ እኮ ነው! ኢሕአፓ ውስጥ የነበረም ሆነ ዛሬም ያለ ማንም ሰው ኢያሱ አለማየሁ የጋራ አመራር ባለበት ድርጅት ውስጥ ተቀምጦ በግሉ ምንም የፖለሲ ውሳኔ በራሱ ሊወስን እንደማይችል እየታወቀ በሱና በጥቂት የአመራር አባላት ላይ የሚዘመተው ለምንድር ነው? የድርጅቱን አባላት ችሎታ መጠየቅ? ሌሎች የአመራር አባላትን መስደብ? ሕብረተሰቡን መናቅ? ወይንስ ተንኮል?

ይህም ማለት በተለያየ ምክንያት ከድርጅቱ ውስጥ ወጥተን የተቀመጥን ወገኖች የምንደረድራቸው ቅሬታዎች መሠረት (ዕውነትነትም) እንኳ ቢኖራቸው ተወደደም ተጠላ ያ ቅሬታ መስተናገድ የነበረበት ወይም ያለበት እዚያው ድርጅቱ ውስጥ ብቻ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ከድርጅቱ ውጭ ኃላፊነት በጎደለው ዓይነት የሚካሄድ ዘመቻ በእኔ ዕምነት አጠያያቂ እየሆነ ከመጣ

ሰነባብቷል። አዎን የምሰማው ክስ ድርጅቱ ውስጥ ይህንን ቅራኔ የማስተናገድ ባሕልም ሆነ መድረክ የለም ነው። ታዲያ እኮ ያንን ባሕልና መድረክም መገንባት የለውጥ ፈላጊው ኃላፊነት ነው። የድርጅቱን ጥንካሬ የሚሻ ደግሞ ለድርጅቱ የውስጥ አንድነት ጥንቃቄ ያደርጋል። እንቅስቃሴው እኛ ብቻ ልክ ነን ሌላው ዲያብሎስ ነው በሚል ግርግር ብቻ ጋጠ ወጥ በሆነ ዓይነት በእልህ የሚገፉ ከሆነ መጨረሻው ዛሬ የምንመለከተው ዓይነት የማያባራ ክስና ንትርክ ሆኖ ይቀራል እንጂ ምንም አይፈይድም። ያ ደግሞ እንግዲህ ሁላችሁም በተለያየ ምክንያት ትግሉን ትታችሁ ብትሄዱም እኛን ለቀቅ አድርጉን፣ ያለንን ይዘን እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሳችን ትግላችንን ቀጥለናል የሚሉትን በድርጅቱ ዙሪያ ያሉትን እድገት ያጫጫል፣ ተስፋ ያስቆርጣል፣ በተለየ ጥቃቱ ጓዶች ነበርን ከሚሉ ሲሰነዘር ልብ ያደማል። ዓላማው ያ ካልሆነ በስተቀር በትግሉ ላይም የሚያደርሰው ጉዳት ደግሞ ከፍተኛ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ ጠንክሮ እንዲሄድ ነው የምንታገለው ለሚሉን እንቅስቃሴዎችም ድርጅቱ ተሰሚነት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ሁናቴዎችን በመፍጠር የተፈለገው ለውጥም ሆነ ዕድገት ይመጣል ማለት ራስን ማሞኘት ነው። የሚፈለገው ለውጥም ሆነ ዕድገት የውሃ ሽታ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው። ኢሕአፓ-ዴ ብለው የወጡት እኮ ዛሬ ተሰነጣጥረው በዘር ሳይቀር ተቦጫጭቀው እስከሚያስገርመን ምንነታቸውን አሳይተውናል። ዛሬ እኮ ኢሕአፓ-ዴ የሚባሉት ከዚያችው ብሶ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ሲወዛወዙ የምናየው። የታለ ታዲያ ያኔ ቃል የገቡልን ጠንካራ ሆነን እንወጣለን ወሬ? ያኔ ድርጅቱን ሲከሱበት የነበረው ሁሉ ምነው ታዲያ በሥራ አልታየ? ወሬና ተግባር የተለያዩ ናቸው። በዚህ ግር ግር የሚጠቀመው ግን ፀረ-ኢትዮጵያዊው ወያኔ ብቻ ለመሆኑ ልንጠራጠር አይገባም። ለዚያ ደግሞ በመጀመሪያ ሃላፊነቱ የሚወድቀው በከሳሾቹ፣ ኢሕአፓ-ዴ፣ ኢሕአፓ ትንሣኤ እና ኢሕአፓ እርማት እንቅስቃሴ ነን ብለው በእኔ አስተያየት የማያባራ የውሸት ጦርነት በመክፈት ባደባባይ በድርጅቱና በጥቂት አመራር አባላት ላይ በሚዘምቱት ላይ ብቻ ነው። እስኪ ይሄን የምልበትን ምክንያት ላብራራ፦

እንደ ምሳሌ እኔ አቶ ሰውየው በዚህ ባለሁበት በምዕራቡ ዓለም በምሥራበት መሥሪያ ቤት እድገትና ታዋቂነትን እንዳገኝ አማራጭ የአሠራር ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዕቅድ ላውጣ እንበል። በመጀመሪያ መረዳት ያለብኝ በምሠራበት መሥሪያ ቤት ተቀጣሪ ሆኜ መቀጠል ይኖርብኛል። ሌላው ደግሞ ይህ ዕቅድ ምንም እንኳ የተሻለና ለምሠራበት ቦታ ብዙ ገንዘብ ሊያድንላቸው መቻሉን የማሳምንበት የተጨበጠ ማስረጃ በእጄ ላይ ቢኖረኝም፣ ያለኝን ዕቅድ በበላይ አለቆቼ ፊት አቅርቤ ላስረዳ የምችልበትን ሁናቴ ማመቻቸት አንዱ ኃላፊነቴ መሆኑን መረዳት አለብኝ። ይህም ዕቅድ በእጄ አለ ብዬ ባለትልቅ ዕውቀት፣ ባለትልቅ ችሎታ ከኔ ሌላ ማን አላችሁ በሚል ማንአህሎኝነት ጭንቅላቴን አሳብጬ ለቅርብ አለቃዬ እንኳን አልታዘዝም በማለት የዕዝ ሠንሰለት ላፈርስ አልችልም። ሌላው ቀርቶ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በትንሽ በትልቁ አልጋጭም። የግል ተደማጭነትና ተአማኒነት በድርጅቱ ውስጥ የሚመሠረተው በዕውቀትና በችሎታ ብቻ ሳይሆን ከሥራ ባልደረቦቼና አለቆቼ ጋር በየደረጃው የምፈጥራቸው ግንኙነቶችም ትልቅ ሚና እንዳላቸው ለማመልከት ነው። አመኔታ ደግሞ በአንድ ምሽት የሚገነባ ሳይሆን በተግባር በጥንቃቄ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ማወቅ ደግሞ ለውጥ እናመጣለን ከሚሉ ወገኖች የሚጠበቅ ዕውቀት ነው። በእኔ በኩል የሚጠበቅብኝን ካሟላሁና ዕውቀቱም ማስረጃዎቼም በእጄ ኖረው የበላይ አለቆቼን ማሳመን ከቻልኩ ያቀረብኩት ሃሳብ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የተሻለ ሆኖ ከተገኘ በሥራ ላይ በሙከራም እንኳ እንዲውል ሊፈቀድልኝ ይችላል። ኢሕአፓ-ዴ፣ ኢሕአፓ ትንሣኤ እና ኢሕአፓ እርማት እንቅስቃሴን ስንመለከት ሁሉም ራሳቸውን ከድርጅቱ ውጪ አስቀምጠው በሌሉበት ቦታ ድርጅት ውስጥ ለውጥ እናመጣለን ሲሉን ለምን ብለን እንስማቸው? እንዲያውም ይህንን በማለቴ የሚቀርብብኝ ክስ አንተ ምናገባህና? ሊሆን ይችላል። ድርጅቱ ውስጥ የለበህበትም ለማለት ነው። መልሴም የሚሆነው እናንተም እኮ ድርጅቱ ዉስጥ የላችሁበትም ነው። ትልቁ ጥፋታችሁም በድርጅት ውስጥ የነበራችሁን መብት ጣጥላችሁ በመውጣት መሰረዛችሁ እኮ ነው! ምነዋ ይሄንን መረዳት አቃታችሁ? ነው የሚሆነው።

እንደ ኢሕአፓ ዓይነት በትግል ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ደግሞ ብዙ የሚጠበቅብን ኃላፊነት፣ ግዴታና ተጠያቂነትም አለ። በተለይ ከድርጅቱ ታሪካዊ ትግልና ካስከፈለውም መስዋዕትነት አንፃር አባላት ተጠራጣሪዎች ቢሆኑ አልፈርድባቸውም። ስለሆነም በድርጅቱ ውስጥ ለውጥ እናመጣለን የሚሉ ተራ አባላትም ሆነ የአመራር አባላት ታማኝነታቸው በጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ኃላፊነቱ የነሱ እንጂ የሌላ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም አቀራረባችን፣ የማሳመን ችሎታችን የአባላትን በጊዜው ያለውን ነባራዊ ችሎታና ስሜት በሚዛን ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። ግልጽነት፣ ዕውነተኝነትና፣ አርቆ አስተዋይነት የለውጥ ፈላጊዎች <u>መሠረት</u> ነው። እኔ ልክ ነኝ ሌላው ዕብድ ነው አይሠራም! እስኪ በኢሕአፓ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ እንፈልጋለን የሚሉን ወገኖች የሚንቀሳቀሱበት ሁናቴ ችግሩ የት ላይ ነው? ገንቢ ወይስ አፍራሽ ? አቋምስ መወሰድ ያለበት ለምንድር ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች በራሴ በኩል ደግሞ መነገር ያለበትን አንዳንድ ልበል።

ይቅርታ ይደረግልኝና የኢሕአፓ ዕርማት እንቅስቃሴ ነን፣ የኢሕአፓ ትንሳኤ አጠናካሪ ነን ኢሕአፓ ዴ ነን የሚሉን አንጃኞችና አፍራሾች የናንተን አላውቅም እንጂ በበኩሌ ወያኔ ወያኔ እየሸተቱኝ ከመጡ ቆይተዋል። እዚህ እንደምታ ላይ የደረስኩት ደግሞ ሌሎች አላምጠው በሰጡኝ ሳይሆን እነዚሁ ወገኖች ባደባባይ ሳይቀድሙኝ ልቅደም ዓይነት ከጠላት ባልተናነሰ ባከታታይ በኢሕአፓና አመራሩ ላይ የሚያደርጓቸውን ዘመቻዎች በመመልከት ነው። ያ ደግሞ ለሁሉም ግልጽ ነው። አዎን! ይህንን ስላልኩ እነዚህን ወገኖች ላላስደስት እችላለሁ። ዕውነታው ግን ተሸፍኖ በይሉኝታ እየተግማማን መኖር አንችልምና ይቅርታችሁን ሊባሉ ይገባል። በተለይም ከላይ ያቀረብኩትን በድርጅት ውስጥ ለውጥ የማምጣት እንቅስቃሴ ጥንቃቄን በተመለከተ ምንም ደንታ የሌላቸውና የማይታወቅ መስሎአቸው የተለያየ አጀንዳ አንግበው ስለድርጅቱ መጠንከር አዛኝ ቂቤ አንጓች በመምሰል የሚነዙብን የውሸት መዓት እንደሆነ ደጋፊ ነን የምንል ሁላ ልናጋልጥና ወግዱልን ልንላቸው ይገባል።

<u>ኢሕአፓ ነበርኩ ማለትና ኢሕአፓ ነኝ</u> ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ተወደደም ተጠላ በኢሕአፓ ውስጥ ለውጥ ማምጣት የሚችሉት፣ የዕርማት እንቅስቃሴውንም የማጠናከሩንም ሁሉም ነገር መሆን የሚቻለው እዚያው ኢሕአፓ ውስጥ በአባላቱ ታታሪነትና ሥራ ብቻ ነው። እንደገንቢነት ሊታይ የሚችለውም ያ ሲሆን ብቻ ነው። ዛሬ ዛሬ የምናየው የድሮ መሪዎች ተብዬዎችም ሳይቀሩ ወይም ደግሞ ኢሕአፓ ነበርን ባይ ቀባጣሪዎች በየራዲዮ ጣቢያና በየኢንተርኔቱ እየወጡ ኢሕአፓን ጥንብ እርኩሱን እያወጡ ድርጅቱን እንደ አዲስ አጠናክረን አናቋቁማለን ብሎ ባዶ ፉከራ ማሰማት ብቻ ነው። ያ ባዶ አዘናጊ ስብከት ደግሞ "ሰዶ ማሳደድ ያማረው ዶሮን በቆቅ ይለውጣል…" የሚለውን የአባቶች ብሂል ያስታውሰኛል። በፍርሻ የተካኑ፣ ሲገነቡ ያልታዩ ወሬኞችን ለምን እንመን? በዓመት እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብሎ የሽምቅ የውሸት ወረቀት መበተን ለውጥ ፈላጊነት ሰይሆን አፍራሽነት ነው። ለኔ ደግሞ ያ ወያኔነት ነው። ወያኔ በሀገር ቤት ባሉ የፖለቲካም ሆነ የብዙሃን ድርጅቶች የራሱ ሰዎች በአመራር ካልመጡ ድርጅቶችን ማመስ አለያም የራሱን ክሎኖች እስከ መፍጠር የደረሰበት አሠራር አለው። ብዙ ገንዘብም ያፈስበታል። የወያኔ መሠረቱ ከፋፍለህ ግዛው ንውና። የሰሞኑን የወያኔ ትዕይንት ለሚመለከት ከዚህ ለማለት የፈለጉትን በቀላሉ ይረዳል ብዬ እገምታለሁ።

በውጪም ኢትዮጵያውያን ያሉበት ድርጅቶች ሁሉ የሃይማኖር ሳይቀር የሚታመሱት በየድርጅቱ ውስጥ በተሰገሰጉ እበላ ባዮች ለመሆኑ ጠንቋይ መቀለብ አያሻም። አሁን አሁን ደግሞ የቀድሞ ኢሕአፓ፣ ኢሕአወሊና ኢሕአሠ አባላትንም ልንሰበስብና ኢሕአፓን እንደ አዲስ ልናደራጀው ነው የሚል ስብከትም በሰፊው እየቀረበልን ነው። ምናለ ሞኞች ከተገኙ ያንን ቲያትር ምናልባትም በሚመጠው በጋ በዋሺንግተን ዲሲ ከሚደረገው የኳስ ጨዋታ ጋር ተያይዞ የሚቀርብልን የዝግጅት እንቅስቃሴ ተጀምሮም ሊሆን ይችላል።

ኸረ እየተስተዋለ ወገን! የቀድሞ የምትሉን ለመሆኑ እነ ማንን ነው ጎበዝ? በዘር በመንደር በወያኔ መንገድ የነጎድነውን? ከወያኔዎች ጋር እየተሻሸን ያለነውን? ወይንስ አንደኛውን እነ በረከት ስምዖኖችና አዲሱ ለገሠዎችን ሁሉ የሚያካትት ነው? ወይንስ ላለፉት 35 ዓመታት ተኝተን፣ ከትግሉ ራሳችንን አርቀን፣ የየግል ኑሮአችንን ስናደላድል የኖርነው የኔ ቢጤዎች ተሰባስበን ቢያንስም ቢጎድልም በድርጅቱ ውስጥ ቆይተው እየታገሉ ያሉትን ወደ ጎን ገፍትረን እኛ ነን ኢሕአፓዎች ብለን ብቅ ልንል? ይሄስ ትክክል ነው ብለን እናምናለን? በየትኛውስ የሞራል ብቃታችን? በየትኛውስ ችሎታችን? የድሮ ኢሕአፓዎች የምትሉን እኮ በምዕራቡ ዓለም ከመጣን ጀምሮ እንኳንስ ለትግሉ በድርጅት መሰባሰብ (ኢሕአፓንም ብንተወው) ሌላ ድርጅት እንኳን ስንፈጥር አልታየንም። ሌላው ቀርቶ የምንቀባባርበት የመረዳጃ ማህበር እንኳ ማቋቋም ያቃተን ማፈሪያዎች ነን ከራሴ ጀምሮ። በተገናኘን ቁጥር ኢሕአፓ ምን አደረገ? ለምን ሕዝቡን ወጣቱን ማሰባሰብ አቃተው ብለን ስናጣጥለው ከመሰማት በስተቀር ስንቶቻችን ነን በአጋርነት እንኳ ለመቆም የጣርነው? አመጣጣችንስ እንዴት እንደሆነ ተረድተነዋል? ወይንስ ከኛ በፊት ቀድመው ወደ ውጪ የወጡት የሠራዊቱ ኮማንደርና የፖለቲካ መሪ ሰሞኑን በሰሜን አሜሪካ ታሪክ ልንጽፍ ነው እያሉ በንቀትና በድፍረት በየከተማው እየሰበሰቡን ሊሰብኩን እንደሚሞክሩት እኛም በፊናችን ሁላችንም የትግሉ ሕየወቴን አብረን ዘምረን ትግሉን ጣጥለን እንኳ ብንመጣ ተስፋ ሳያስቆርጣቸው ትግሉን የቀጠሉትን ታሪክ ሳይቀር ካለ ሃፍረት ሽሚያውን መያያዙ ይሻለናል? ዛሬ ዛሬ ከመቃብራችን አፋፍ ላይ ቆመን ትግሉን ትተን የመጣነው በአመራሮቹ ምክንያት ነው እያልን አደራ በላነታችንን ለመሸፈን እየተሯሯጥን ይህችን ዓለም ልናልፋት ነው ማለት ነው? ወይስ የጀመርነውን ትግል አብረን ከዳር ለማድረስ ቆርጠን መነሳታችንን በተግባር ከድርጅቱ ውስጥ ሆነው ያቅማቸውን ከሚያደርጉት ጎን ለመሰለፍ ለራሳችን ቃል በመግባት ወይ በመርዳት አለያም በመቀላቀል ከሕዝቡ ልንወግን? እነሂህ በትግሉ ሜዳ ህየወታቸውን ያሳለፉትን ወገኖች ቁም ስቅል ስናሳይ ችግራችን ምንድር ነው? ለምን ትግሉን ቀጠሉ? አስቀጠሉ? እኛስ በእኛነታችን የምንቀበለው ኃላፊነትስ ምንድር ነው ብለን ከራሳችን ጋር ተነጋግረን እናውቃለን? ወይም አንዳንዶቻችን እንደምናደርገው ጣጥለን ስንነጉድ ወደኋላ ቀርተው ትግሉን ያስቀጠሉትን የፈረደባቸውን ጥቂት ጀግና መሪዎችና አባላት እየረገምን እስከ ዕለተ ሞታችን ጣቶቻችንን እንደ ቀሰርን ልናልፋት? ኸረ ፊታችንን ከመስታወቱ ፊት እናድርግና ራሳችንን እንገምግም ጎበዝ! ብዙ ምክንያት አንደርድር!

**ለማጠቃለል፥**

በኢሕአፓ ውስጥ ተሰባስበው ትግሉን ላስቀጠሉ ወገኖች ከፍተኛ አክብሮትና አድናቆት አለኝ። ኢሕአፓዎች ከውጭ በሚሰነዘርባቸው ቅጥቀጣ በውስጣቸው ጨለምተኝነት እንዲነግሥ፣ በራስ መተማመን እንዲጠፋ የኢትዮጵያዊነት ጠላቶች በየአቅጣጫው የሚሰነዘሩባቸውን ጥቃት ተቋቁመው፤ ኢሕአፓ ነበርን በምንልም ጭምር አፍራሽና ቅጥ ያጣ ዘለፋ እየወረደባቸው ዘሬም በትግሉ ውስጥ እነሆ ለ 42 ዓመታት መቀጠላቸው የሚያስደንቃቸው እንጂ የሚያስኮንናቸው ከቶውንም ሊሆን አይችልም። ይህን ኢትዮጵያዊ ድርጅት ለማጠናከር እፈልጋለሁ የሚል ወገን ሁሉ ከውጭ ሆኖ ቅስም የሚሰብር ትችት ማዥጎድጎድ ሳይሆን ለድርጅቱ ታማኝነትን ገንብቶ በቅንንነት ከድርጅቱ ውስጥ ገብቶ የፈለገውን ለውጥ ማምጣት የተገባ ነው። ካለያም ደግሞ ታማኝ ደጋፊ ሆኖ ከውጪ የሞራልም ሆነ የቁሳቁስ ዕርዳታ እያደረጉ አይዞአችሁ ማለትም ይቻላል። አንድ ሰው ደግሞ ራሱን በታማኝነትና በቅንነት ካቀረበ የድርጅቱ አባላትም ሆነ አመራር በዚህ ደረጃ ያሉ ግለ ሠቦችን ገንቢ ሂስ አይቀበሉም ማለት ይከብደኛል። የውሸት ነጎድጓድ እያዘነቡ የሚተቹትን የድርጅቱ አባላት ባይሰሟቸው አልፈርድባቸውም። የድርጅቱ አባል ነበርኩ ወይም አለሁበት በሚል ሽፋን የሚደረግ ጸረ-ድርጅት ዘመቻ ግን በፍጹም ገንቢነት አይደለም። ኢሕአፓነትም አይደለም። ድርጅቱ የሚሄድበት አቅጣጫ አላማረኝም፣ ወይም ትግል በቃኝ ወዘተ. ብለን ድርጅቱን ጥለን ከወጣን በኋላ ግን የሚጠበቅብን እንዲያው <u>ዝምምምም</u> ብቻ ነው። ድርጅቱን ከወያኔ ባልተናነሰ ሁናቴ መታገል በየትም ብትመዝኑት ለኔ ወያኔነትና ቅሌት ነው።

እምቢኝ ለዘረኝነት፣ ለበታኞችና፣ ለባንዶች!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!


ሀቀኛ መሪዎቻችንና ድርጅቶቻችንን እንደግፍ!

አስመሳይ መሪ ተብዬዎችንና አፍራሾችን ሳንፈራ እናጋልጥ!

አቶ ሰውየው (ከሰሜን አሜሪካ - የካቲት 1 2007)
(February 7, 2015)

# የሰረቁት ስጋ ያስይዛል መረቁ

## (የሐማ ቱማ ድብቅ ሴራ)




በወያኔ ኢ.ህዴግ "ተቃዋሚነታቸው" ለረዥም ዘመናት የሚታወቁት የአቶ እያሱ አለማየሁ መጽሃፍ ባላንጣዎቼ የሚኗቸው ባለስልጣናት በተገኙበት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል መመረቁ ተሰማ፡፡

The Case of the Socialist Witch doctor በመባል የሚታወቀው የአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ መጽሐፍ የሶሻሊስቱ ጠንቋይ ጉዳይ በሚል ርዕስ በአማርኛ ተተርጉሞ አዲስ አበባ ውስጥ December 27, 2014 ቀን የወያኔ ባለሥልጣናት በተገኙበት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ተመርቋል።

የመፅሀፉን በኣዲስ ኣበባ መታተምና በተለይም የወያኔ ቱባ ባለሰልጣናትና ጀሌዎቻቸው ዋና መናኸሪያ በሆነው በዋቢሸበሌ ሆቴል መመረቁን አስመልክቶ ለተነሳው ጥያቄ አቶ ኢያሱም ሆኑ በእሳቸው የሚመራው "ኢሕአፓ" ምንም ዓይነት መግለጫ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑም ። እንደውም ይባስ ብለው በደጋፊዎቻቸው ድህረ ገጾች የመጸሐፉን ግምገማ አሰራጭተውት ይገኛል።

ስለ ዋቢ ሸበሌው ዝግጅት ይህንን ድረ ገጽ ይመልከቱ። http://www.borkena.com/2014/12/27/the-case-of-the-socialist-witchdoctor/

ኢሕአፓን በመክፈልና አባላትን ወያኔ እያሉ በመፈረጅ የሚታወቁት አቶ ኢያሱ ከወያኔ ጋር እንዲህ የቀረበ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይችላሉ ተብሎ አይገመትም ነበር። ይሁንና ዛሬ ጽዋው ሞልቶላቸው ፓሪስ አገር በምትኖር አንዲት ጋዜጠኛ አማካኝነት ድርድር እንዳደረጉና እንደተሳካላቸውም ይነገራል። አቶ እያሱ ይህን ሲያደርጉ መቸም ያምራል ብለው ለነብር ልጅ እዳኑ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይሁን እንጅ ወያኔ የነጻውን ፕረስ ሰዎች ፣ ታጋዮችን ከውጭ ሳይቀር እያፈነ በሚያስርበት በአሁኑ ወቅት አቶ ኢያሱ መጽሐፍ እያተሙ መሐል አራዳ አዲስ አበባ ላይ ሲሸጡ መታየቱ አጀብ ከማለት ውጭ ሌላ ምን ይባላል። መቸም አንዳች የውስጥ ነገር የድርጅት ሥራ! እንደሚባለው አይነት ስምምነት ቤጤ! ሳይኖር በትግል የተገኘ ድል ነው ማለት ከቶ አይታሰብም። ሳይሰድብህ ስደበው፣ በሚል ዘዬ አቶ ኢያሱ "እንጻፍ ከተባለማ" በሚል ጽሁፋቸው ሁሉን ወያኔ ሲሉ ከርመው ዛሬ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል መጽሐፍ ማስመረቃቸው ሲሰማ ምን ሊሆን እንደሚችሉ መገመት ከቶ አያዳግትም።

ቀደም ሲል ከወያኔ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት የመጽሐፉ ህትመትና ምረቃ እንዳይደናቀፍ በማሰብ በባሕር ዳር የተደረገውን የንፁሃን ዜጎቸ ጭፍጨፋ የሚያወግዝ መግለጫ ድርጅታቸው "ኢ.ሕ.አ.ፓ" እንዳያወጣ አቶ ኢያሱ እስከአሁን ድረስ ማገዳቸው

ለአብነት የሚጠቀስ ዋቢ ነው። ይህንን በሚመለከት በድህረ ገጻቸው መመልከት ይቻላል። ለዜጎች ደህንነትና መብት ሲታገል የኖረና አያሌ መስዋእትነት የከፈለበትን አብይ ሀገራዊና ህዝባዊ ዓላማ ዛሬ በአንፃራዊነት ወደጎንን ገለል የመደረጉና ዜጎች ያለአግባብ በዘረኞች ሲጨፈጨፉና ሲገደሉ ማውገዝ እንኳን ያልተቻለበት ሁኔታ ላይ መደረሱ፤ ወያኔ የሚፈፅመዉን አይነተኛ የግፍ ተግባር ከመደገፍ ያለፈ ሌላ ምን ሊባል ይቻላል? በተለይ በእያሱ የሚመራው " "ኢሕአፓ" ደጋፊዎች ይህንን በተመለከተ ምንም ተቃውሞ አለማሰማታቸው በብዙዎች ዘንድ አግራሞትን ፈጥሯል። በቅርቡ የኢያሱ "ኢሕአፓ" የቡርኪና ፋሶን ትግል ይደግፋል" የሚል መግለጫ እንዳላወጣ ሁሉ፣ በባሕር ዳር ለተጨፈጨፉት ኢትዮጵያዉያን ወገኖች አንዲት ቅንጣት መግለጫ ማውጣት የተሳነው ድርጅት ሆኖ የመገኘቱ ጉዳይ፣ ከባህርዳር ይልቅ የቡርኪ ናፋሶ ጉዳይ ያሳሰበው ይመስላል።

የእነ ጸጋዬ ደብተራውን፣ የነ ጋይም፣ የነ ይሰሃቅ ደብረፅዮን፣ የነ ስጦታው ሁሴን ወዘተ ገዳይ ከሆነው ወያኔ ጋር ለአንድ መጽሐፍ ተብሎ እየተሞዳሞዱ የዜጎችን ገህድ የወጣ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ማውገዝ አለመቻል ለኢ.ሕ.አ.ፓ ለዘመናት በታጋዮቹ ደም የገነባውን ዝናና ክብር ከማቆሸሹም ባሻገር፣ ሃገርና ሕዝብን የመካድ አይነት አሳፋሪ ተግባርም ጭምር ነው የሚሆነው። " በኢሕአፓ" ስም መነገድ ካሁን ወዲያ ማክተም አለበት ። ከአቶ ኢያሱ ጋር በመወገን በተሳሳተ መስመር ያላችሁ ይህ ጥያቄ መልስ እስካላገኘ ድረስ ራሳችሁን ከዚህ የክህደት አባዜ ነፃ መሆን ከቶ አትችሉም። ድርጅቱንም ሆነ ትግሉን አዘቅት ውስጥ ከማስገባታችሁ በፊት ላፍታ ቆም ብላችሁ ራሳችሁንንና ሥራችሁን ትፈትሹ ዘንድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ትጠየቃላችሁ።

አቶ እያሱ በድርጅቱ ውስጥ እንዳሻው ሲፏልሉ የመኖራቸውን ያህል በአሁኑ ወቅት ደግሞ እየተንዘባዘቡ የድርጅቱን ዓላማ በመጣስ ህልውና በሚፈታተን ተግባር ላይ ተሰማርተው የመገኘታቸው ጉዳይም ሆነ የለዘብተኝነት አቋም ካላቸው ጋሻጃግሬዎች አንፃር ሲመዘን ፦

" እረ' ምን ሞኝ ነው፡ እረ' ምኑ ጅል ነው፤<br>
ሲሰድቡት ዝም ያለ ቢመቱትም ያው ነው።" .... የሚያሰኝ ሆኗል።

የአቶ እያሱ አለማየሁ ያሻቸው በድርጅት መሪነት እንዲያም ሲል በተራ አባልነት እየተሰየሙ በተለያዩ ድህረ -ገፆችና ሚዲያዎች በርካታ ነጥቦች እያነሱ እንዲህና እንዲያ ሲዘላብዱ መቆየታቸው ይታወቃል። ከዛም ባሻገር ሲፈልጉ በስማቸው አለያም በብዕር ስሞች ብዙ ጉዳዮችን ሲያስደምጡን ኖረዋል፡፡ በአለፈው ዓመት በጠንካራ የኢህአፓ አባላት ጥረት በጉባኤ እስከሚወሰን ድረስ የታገዱ መሆናቸው ቢታወቅም፣ አሁን ደግሞ በማናለብኝነት እንዲህ ያለ የንቀትን የክህደት ተግባር በይፋ መፈፀማቸው የኢ.ህ.አ.ፓን ግብዓተ መሬት ለማፋጠን ቆርጠው የተነሱ ይመስላል፡፡

አቶ ኢያሱ የኢህአፓ አባላትን እየከፋፈሉና እርስበርስ እያጋጩ ድርጅቱ አሁን ካለበት ደረጃ ማድረሳቸው ብቻ ሳይበቃቸው ህልውናዉን ለማጥፋት የተቻላቸውውን ያህል አድርገዋል እያደረጉም ነው ማለት ይቻላል። የኢህአፓ በጠንካራ አባላት ገንዘብ የቆመ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፡ አባላቱ ድጋፍ ከመስጠትና ገንዘብ ከማዋጣት በስተቀር በድርጅቱም ይሁን በአመራሩ ዙሪያ ምንም ዓይነት ጥያቄዎችን እንዳያነሱ ሰንጎ በመያዝ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዚያም አልፎ ደፍረው ወሳኝ ጥያቄ ያነሱ ጠንካራ አባላትን ክድርጅቱ እንዲባረሩ እስከማድረግም የደረሰ ሰው ነው። ከድርጅቱ ሕገ - ደንብ ውጭ በስሙና ደጋፊ ጀሌዎቹ በሆኑ ድህረ ገጾች እየታገዘ የማይታወቅ መስሎት የበርካታ ነባር የታጋዮችን ስም ሲያጎድፍና

ሲያጥላላ መቆየቱ ይታወቃል። ተስፉ የተጣለበት የታሪክ ተረካቢውና የድርጅቱ የጀርባ ኣጥንት የሆነውን የወጣት ክንፍ የኣመራር አባላትን እስከማባበር የደረሰ እብሪተኛና ኢዲሞክራት ነው። አሁን በስተመጨረሻ ደግሞ እየታየ ያለው ትንግርታዊ ድራማው፣ ይህንን ሁሉ ወንጀል በምን አግባብ እንደሠራውና እየሠራው እንዳለ በሸንጎ ይፋ ያደረገበት የሰሞኑ ያዲስ አበባው የዋቢ ሸበሌ ሆቴል ትእይንት የሁላችንም መነጋገሪያ ለመሆን በቅቷል። የግለሰቡን ወቅታዊ አቋም ለመገመት ከዚህ የበለጠ ማስረጃ መጥቀስ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም።

"የክረምት በቆሎ ጎርፍ የደፈጠጠው፣
ተኝቶ ያፈራል ትል እያላመጠው ።" .... እንዳይሆንና እንዳንተዛዘብ።

ቤቱማ ምን' አርጎ፡ የበላንበቱ፡ የጠጣንበቱ፤
አልጋው ይፍረስ እንጅ፡ ትኋን ያለበቱ። .... ያለው ያአገሬ ገበሬ ወዶ እንዳልሆነ ልብ ይሏል!

ወደፊት አቶ ኢያሱ በኢሕፓና በአባላቱ ላይ የፈጸመውን ወንጀል በማስረጃ የተደገፈ ዶክመንት አንደማቀርብ ቃል አየገባሁ በዚህ ልሰናበታችሁ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል

ኢሕአፓ አንድ ይሆናል!

# ዳግማዊ ጋይም -

# Strange bed fellows: Isayas Afewerki courting Iyasu Alemayehu

ክምችት, ወቅታዊ ሁኔታዎች 24 Jan 2015




A senior political observer of the horn of Africa has uncovered that the Eritrean President Isayas Afewerki has scored a major win in his new strategy of engaging the Ethiopian opposition to stamp out the renewed claim to the sea by increasing number of Ethiopians.

In its latest move, the Eritrean leader has reached an agreement with the Iyasu Alemayehu led EPRP whereby Eritrea will finance or provide a satellite TV program to be broadcast to Ethiopia and in return Iyasu Alemayehu's group will " smoothen " the opposition's fervent assertion of Ethiopia's legal and historical right of access to the sea.

Both Iyasu Alemayehu and Isayas Afewerki see this agreement as a win- win situation. For years now, the Iyasu Alemayehu led EPRP has been literally shut out of the political process among the opposition inside and outside Ethiopia. As well, Iyasu Alemayehu, has been personally accused of perpetrating the negative image of his group.Iyasu believes that access to media will provide him an opportunity to make his presence felt and to overcome the negative public image. He also hopes that this latest move will help to quill the opposition from within his party that has been questioning his leadership.

The Eritrean leader, on the other hand, believes that his support for EPRP will soften the position of those in the Ethiopian opposition camp who see the separation of Eritrea as illegal. The Ethiopian opposition is perceived to be the major hindrance for Isayas Afewerki's strategic goal of securing full agreement on the border demarcation with the Ethiopian government.
Twenty three years has passed since EPLF secured freedom from Ethiopia. However, the opposition to the independence of Eritrea among the Ethiopian public and the major opposition groups continues. This remains to be key concern for Asmara.

The publication of a book few years ago by a prominent lawyer Yacob Haile-Mariam (Ph.D.) entitled “ASSAB YEMANNAT (whose is Assab ) and another book “ Sovereignty and Democracy in Ethiopia” written by the former President of the regional government of Tigray and former member of the executive committee of the ruling EPRDF and TPLF , Gibru Asrat , has ignited a raging debate about Ethiopian’s access to the sea. This latest revival of debate and assertion among Ethiopians is perceived as a serious threat by the authorities in Asmara.

Mr Yemane, Gebreab, a political advisor to Eritrea President Isayas Afewerki and a schoolmate and long-time personal friend of Iyasu Almayehu was ostensibly the deal maker behind this unexpected agreement. It is reported that, at the invitation of Yemane Gebreab, some 10 years ago, Iyasu Almayehu visited Asmara in a bid to win support from the Eritrean authorities. His attempt to establish relationship with the Eritrean leadership was brought to a halt after most of the then leadership of EPRP opposed his proposal.

In the past, Isayas Afewerki has been successful to secure Eritrea’s interest by making friends within the Ethiopian opposition groups. Whether his latest investment in the Iyasu Alemayehu led group will bring consequential change for Isayas remains to be seen.
ethiopanorama@aol.com
← Ethiopia's media crackdown is bad news for Africa' አብዮታዊ እርምጃ – በትግራይ! →

## Leave A Reply

You must be logged in to post a comment.

**Find us on Facebook**

Copyright © 2011 www.ethiopanorama.com
↑ Scroll to top

## ትንሳኤ

### ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!

እኛ የትንሳኤ ስብስብ በተለያዩ ጊዜያት በጽሁፍ፤ በሬዲዮ ብሎም በቴለቪዥን መስኮት ያለንን አላማ ለኢህአፓ አባላቶችና በተለያዩ ምክንያት ከድርጅቱ ለወጡ እንዲሁም በድርጅቱ ዉስጥ ለመታገል ለሚፈልጉ ታጋይ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ በተደጋጋሚ  አሳዉቀናል፤ ዛሬም እንደገና ወደፊት ድርጅቱን ለማጠናከር ተገቢ ናቸዉ ብለን  ለምንመኛቸዉና አጥብቀን ስለምንታገልለት ዴሞክራሲያዊ አካሄድ መተንተኑ ተገቢ ነዉ እንላለን፤፤

አሁንም ቢሆን የኢህአፓ ከሁለት መከፈል እጅጉን አሳዝኖናል፤ አበሳጭቶናልም፤ ይህነዉ የሚባል ወይም መሰረታዊ የሆነ የአላማ፤ የርእዩተ አለምና የራእይ ልዩነት ሳይኖር፤ ብዙ ጓዶች ዉድ ህይወታቸዉን የገበሩበት፤ የቆሰሉለትና የደሙለትን ድርጅት፤ ሃላፊነት በጎደለዉና ከምክንያት ይልቅ በስሜት ተገፋፍቶ፤ በግብር ይዉጣ መልክ ድርጅቱን መከፋፈልና ትግሉን አደጋ ላይ መጣሉ፤ በትንሳኤ ስር የተሰባሰብነዉን ጓዶች አንገብግቦናል አሳስቦናልም፤ ለዚህም ነዉ እራሳችንን አሰባስበንና አጠናክረን በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የሚመራና፤ ከሁላም በላይ ለሰፊዉ ህዝብ የበላይነት የሚታገል የጋራ አንድ ኢህአፓ ለማሰባሰብ ያለምነዉ፤፤

ትንሳኤ የኢህአፓ ልጆች ሲል ከሳሾቻችን እንደሚሉት ለወያኔ ያደረዉን፤  ወይንም የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም አሳልፎ የሰጠዉን፤ አሊያም መስዋትነት የተከፈለበትን የሙብት ጥያቄ የረገጠዉን ሳይሆን፤ የህዝብን ችግር የራሱ አድርጎ የተነሳዉን፤ በሃገር ፍቅር  ስሜት የተቃጠለዉንና፤ የሰማእታትን የትግል አርማ ለመሸከም የሚፈልገዉን፤ አላማ ጽኑ ታጋይ ማለታችን ነዉ፥ ኢህአፓ ይጠናከር፤ ከዉስጥም ሆነ ከዉጭ ያሉትን እናሰባስብ ስንል፤ እነዚያን ለህይወታቸዉ ሳይሳሱ ከጠላት ጋር በመተናነቅ አኩሪ ታሪክ ያስመዘገቡትን፤ በደማቸዉ ታሪክ የጻፉትን፤ በአጥንታቸዉ የኢህአፓን ሰንደቅ ከፍ አድርጎ ለመስቀል ሲሉ እንደወጡ የቀሩትን፤ እሬሳቸዉ በየመንገዱ የተጣለዉን፤ በጅምላ በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩትንና ፤የአዉሬ እራት የሆኑትን ጓዶች በማሰብ ነዉ፤፤

ኢህአፓ ተጠናክሮአል፤ አባላቶችም እየበዙ ነዉ፤ በህዝብ ዘንድም ሰርጾ እየገባ ነዉ፤ለምትሉን መልሳችን፤ ቤታችን ኢህአፓ ሲሞቅና፤ ሲቀዘቅዝ የትግል እሳቱም ሲጋይና፤ ሲዳፈን ነበርንበትና፤ በደንብ እናዉቀዋለን፤ በአሁኑ ሰአት ኢህአፓ መከፋፈልና መዳከም ብቻ ሳይሆን፤ በህዝባዊ ትግሉ ይህ ነዉ ሊባል የሚችል አወንታዊ ዉጤት ባለማሳየቱ፤ እታገልለታለሁ ከሚለዉ ህዝብ ጋር መራራቅ ብቻ ሳይሆን፤ ህዝቡም የኢህአፓን እንደ ድርጅት መኖርና መንቀሳቀሱን በመርሳት፤ ኢህአፓ በተባለ ቁጥር ኢህአፓ ደግሞ አለ ብለዉ የሚጠይቁ ብዙዎች ናቸዉ፤ ስለዚህ ያልተደረገዉን እንደተደረገ በማስመሰል፤ የህልም ዳቦ መግመጡን ትተን፤ ድርጅቱን እናጠናክረዉ እናጎልበተዉ ነዉ የኛ ምክር አላማም፤፤

እንዲያዉም እራሱን ኢህአፓ ነን በሚለዉ ቡድንና፤ ተገንጥሎ ወጥቶ እራሱን ኢህአፓ-ዴ ብሎ በሰየመዉ ቡድን፤ እርቅ ሰላም ለማዉረድ በቅርቡ የተሞከረዉ ጥረት ፍሬ ሳያሳይ በመቅረቱ፤ በጉጉት የጠበቅነዉም የአንድነት ትግል መጀመር በመጨናገፉ ቁጭታችን ከፍ ያለ ነዉ፤ ይህ ሙከራ ግዜ የፈጀ ዉጣ ዉረድ የነበረበት ስለነበረ፤ ዉድ ጊዜያቸዉን አጥፍተዉ ድርጅቱን ለማዳን የደከሙትን፤ ከወዲሁ እያመሰገን ይህን ቀና ሃሳብ የደገፉትን አበጃችሁ ስንል፤ ጀርባቸዉን የሰጡትን ግለኞች ደግሞ ሌላ ምንም ማለት አንችልም፤ የሰማእታት  አጽም ይፋረዳችሁ ከማለት በስተቀር፤ ይህ እርቀ ሰላም ቢሳካ ኖሮ ኢህአፓን እንደ ድርጅት ከማጠናከሩም በላይ፤ በአሁኑ ሰአት የኢትዮጵያ ህዝብለሚያደርገዉ ጸረ ወያኔ ትግል፤ አጋዥም አበረታችም ይሆን ነበር፤ አለመታደል ነዉ እንዲሉ፤ በአመራር ቦታ ያሉትና፤ እርቅ ሰላሙን የተሳተፉት ጓዶች ቅራኔን ከማርገብ ይልቅ ማፋፋምን፤ ልዩነትን አጥብቦ በጋራ ከመቆም ይልቅ ቃላትን በመሰነጣጠቅ ልዩነትን አስፍቶ በተናጠል መቆማና፤ እንደጠላት መተያየትን መርጠዋል፤ ይህ ከድርጅትና ከጋራ ጥቅም ይልቅ ተክለ  ሰዉነትን መገንባት የተጠናወተዉ በሽታ፤ ለድርጅቱ ዉድቀት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝባዊ ትግል  ላይም የማይሽር ጠባሳ እንደሚያሳርፍም ጥርጥር የለነም፤፤

የዛሬን አያድርገዉና፤ ትናንትና በኢድሕቅ የትግል ሂደት ዉስጥ መኢሶን ጎን የተሰለፈዉ ኢህአፓ ዘንድሮ በዉስጡ የተፈጠሩ ችግሮችን በዲሞክራሲያዉ ሁኔታ መፍታት፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ሲባልም ይቅር ተባብሎና፤ ተቻችሎ ትግሉን መቀጠል አለምቻሉ ሁላችንም ያስገረመ ሚስጥር ብቻ ሳይሆን፤ ድርጅቱ ምን ያህል ከዲሞክራሲያዊ  አሰራርና ከምንክንያት ጋር እንደተጣላም ያመላክታል፤ ድርጅቱ የራስ ንብረት ይመስል፤ ሌሎችን ድንጋይ ተሸከመዉ ይቅርታ ካላሉ፤ አይናች ሁን ላፈር ማለት፤ አዋቂነትን ሳይሆን አምባገነናዊ ባህሪን የሚያሳይ ነዉ፤ ስለዚህ ኢህአፓ አብቦና አፍርቶ ለማየት የምንፈልግ ሁሉ ነገሩን በአንክሮ ተመልክተን መወያየትና ለችግሮችም መልስ መሻት ተገቢ ነዉ እንላለን፤፤

ለነገሩማ በአመራር ቦታ ብዙ ጊዜ መቆየት ድርጅትን የግል ንብረት አድሮጎ የማየትንአባዜ ያስከትላል፤ ተመክሮአችን ሁሉ የሶሻሊስት ፍልስፍና ሆነና፤ ሁላችንም ከድርጅት የስልጣን ኮረቻ መዉረድን ወይም ለሚገባዉ ሰዉ ስልጣን መልቀቅ ተገቢ ስርአት አድሮጎ መቀበል ተስኖን፤ እንደወያኔዉ አምባገነን መሪ ሞት ካልወሰድን በስተቀር የሙጥኝ ማለቱን ተያይዘነዋል፥ ድርጅቱን የግል ንብረት አድርጎ መቁጠር ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቻችን የድርጅት አባላትም ጭምር የመለኮትን ያህል እንዲያመልኩን እንሻለን፤ በቅርቡ ከወያኔ አገዛዝ በራሱ ፈቃድ ጥሎ የወጣዉ አቶ ኤርሚያስ ለገሰ፤ የመለሰ ቱርፋቶች በሚለዉ መጣጥፉ፤ ምን ያህል የወያኔዉ ድርጅት የአቶ መለሰ ዜናዊ የግል ንበረት እንደሆነና፤ አቶ መለሰም በድርጅቱ ላይ የነበራቸዉን ያልተገደበ ፍጹማዊ ስልጣን አመላክቷል፤ ስለዚህ እንደዚህ አይነት በድርጅት ዉስጥ የሚፈጠሩ ግለሰብ አምላኪነትና ያልተገደበ ስልጣን መኖርን፤ ሁላችንም ለዲሞክርሲ፤ ለፍትሕና ለእኩልነት የምንታገል ሁሉ ልናወግዘዉ ይገባል፥ በአመራር ቦታ የሚቀመጡ መሪዎች የስልጣን ጊዜያትና ገደብም እንዲኖራቸዉ የግድ ይላል፤ ድርጅቶችም ይህን በተመለከት ህግ ማዉጣት ብቻ ሳይሆን ለተግባራዊነት መታገል አለባቸዉ፤በድርጅት ዉስጥ የታቀፉ አባላትም፤ ከግለሰብ አምላኪነትና ከቡድንነኝት ነጻ በሆነ መንፈስ ሃላፊነታቸዉን መወጣት ይኖርባቸዋል፤ ማንኛዉን አይነት አምባገነናዊ ባህል ማስወገድና በምትኩ የተለያዩ ሀሳቦች ሊሸራሸሩበትና አባላት ያለምን ስጋት ያላቸዉን ልዩነት ሊያሰሙበት የሚችል መድረክ መፍጠር ተገቢ ነዉ፤፤

የአምባገነን ባህል አሜን ብሎ የተቀበለ፤ ስልጣንን ከሃላፊነትና ከተጠያቂነት ማጣመር የተሳነዉና፤ መመረጥንም ሆነ ስልጣን መልቀቅን ማቀናጀት የማይችል ድርጅት እንኳን ህዝብንና አገርን ነጻ ሊያወጣ ይቅርና እራሱንም ነጻ ማዉጣት አይችልም፤ አጋጣሚ ሰጥቶትም ስልጣን ላይ ቢቆናጠጥ ለህዝብ ነቀርሳ እንጅ መፍትሔ እንደማይሆን ወያኔ በአሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርሰዉ ግፍ በቂ ምስክር ሊሆነን ይገባል፤ ስለዚህ የአባላቶች ንቁ ተሳትፎ፤ አዙሮ መመልከትን ብሎም ተላምጦ የተሰጠን ብቻ ከመዋጥ ይልቅ እራስም ማኘክን መልመድ፤ ድርጅትንም ሆነ አገርን ከጥፋት ያድናል፤ አለበለዚያ ግን እነዚያ እንደመልኮት ሲታዩ የነበሩ አመራሮች መምራት ሲያቅታቸዉ ወይም በሞት ሲለዩ ድርጅቱ ሞተሩ እንደተበላሸ ተሽከርካሪ መቆሙ የማይቀር ይሆናል፤፤

ከዚህ ባሻገር በቅርቡ ስለወጣዉ የኢህአፓ-ዴ እና እርማት እንቅስቃሴ ስለ ተባለዉ ቡድን የጋራ መግለጫ በኢንተርኔት ድረገጽ ተመልክተናል፤ በጥቅሉ ጅማሬዉንና፤ ጽንሰ ሃሳቡን የምንደግፈዉ ቢሆንም በ አሰራሩ ላይ ግን ልዩነት አለን፤ በቅድሚያ በጥሪዉ ሆነ በመሰናዶዉ የኢህአፓ ጉዳይ ይመለከታቸዋል የተባሉትን ሁሉ ማሳተፍ ተገቢ ነዉ፤ በተለይም በአሁኑ ሰአት የተለያዩ ቡድኖችም ሆነ ግለሰቦች ኢህአፓን አንድ ለማድረግ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ከወዲሁ እነሱን ማማከርና በሂደቱ እንዲሳተፉ መጋበዙ ተገቢ ሆኖ እያለ፤ አንዱ ቡድን ሌላዉን ጥሎ ለማለፍ የሚያደርገዉ ግብግብ ዉጤታማ ሊሆን አይችልም፤ ትንሳኤም የተነሳለት አላማ ግብግቡ ቀርቶ ሁሉም ጓዶች በሰከነና አስተዋይነትበተሞላበት ሁኔታ ችግሩን በአንክሮ ተመልክተዉ መፍትሔ ላይ እንዲደርሱና አንድ ኢህአፓን ይዘዉ እንዲወጡ ስለሆነ አላማችን፤ ከወዲሁ አሰራሩ ሁሉንም እንዲያቅፍ እናሳስባለን፤፤

ኢህአፓ በተባበረ ክንዳችን ይጠናከራል፡-
የኢትዮጵያ ህዝብ ያቸንፈል፡-

# ኢህአፓ ዴሞክራሲያዊና የኢህአፓ እርምት እንቅስቃሴ በአንድ ኢሕአፓ ጥላ ሥር ሆነው ለመታገል የሚያስችል ጉባኤ ለመጥራት ተስማሙ።

12/21/14

ከዚህ በፊት ባወጣናቸው የጋራ መግለጫዎች ኢህአፓ ዴሞክራሲያዊና የኢህአፓ እርምት እንቅስቃሴ የጋራ ኮሚቴ አቋቁመን ውይይት እያደረግን መሆናችንን ገልጸን ነበር። አሁን ደግሞ ሁለታችንም <u>**ኢህአፓን አንድ አድርገን**</u> ከመታገል ውጭ ሌላ አመራጭ እንደሌለ ተማምነናል። ከዚህ ስምምነት እንድንደርስ ከአደረጉን ዋና ዋና ምክንያቶችም

1ኛ ገና ትግሉን ስንጀምር ይዘነው የተነሳነው ዕራይ አሁንም ሁኔታው የሚጠይቀው በመሆኑ

2ኛ. እንዲሁም ድሮ ለሕዝባችን የጠየቅነው የዴሞክራሲና የሰብዓዊነት ጥያቄ አሁንም ድረስ ያለተመለሰ በመሆኑ

3ኛ የአገራችን ሁኔታ ከምን ጊዜውም በበለጠ በከፋ ሁኔታ ላይ በመገኘቱና ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚቻለው ተጠናክሮ በመታገል እንጅ በመከፋፈል አለመሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።

እየከፋ ለመጣውን የአገራችን የፖሊቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ቀውስ መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው ተባብሮና ተጠናክሮ መታገል ታሪካዊ ሁኔታው የግድ ይላል። ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ሕብረተሰባችን በመሬቱና በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት ተነፍጎት፤ የዴሞክራሲ ጥያቄ አንስተው በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች፤ የነጻ ጋዜጣ አዘጋጆችና ብሎገሮች ወደ እስርቤት የሚወረወሩባት አገር ናት። አያት ቅድማያቶቻችን በደምና በአጥንታቸው አስከበረውት የኖሩትን የአገራችን መሬት ለሱዳን ዳርንጎት ተቆርሶ የተሰጠበት ሁኔታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ እንደ እግር እሳት የሚያንገበግብበት ወቅት ላይ ነን። በልማት ስም ያለምንም ቁጥጥር የውጭ ከበርቴዎች የአገራችን ለም መሬት በመቀራመት በቦታው ላይ የሚኖሩትን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች እያፈናቀሉ ቤት የለሽ እያደረጓቸው ነው። የድህነት ደረጃ ጣራውን ነክቶ ከገጠር ከቀያቸው የተፈናቀሉ፤ በከተማ ከሥራ የተባረሩት እና ትምህርታቸውን ጨርሰው ስራ ያጡ ወጣቶች በአገሪቱ ዋና ዋና ከተማዎች በረንዳ አዳሪ ሆነዋል። “ምርት ተትረፍርፋል፤ 11% አድጓል፤ ከአፍሪቃ አገሮች በኢኮኖሚ ዕድገት በአንደኝነት እየመራን ነው” ሲል የከረመው አሁን ሰሞኑን በአገራችን ርሃብ ገብቷልና የዓለም እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች

ድረሱልን ማለቱን ስንሰማ ድሮንስ ከአምባ ገነን መንግሥት ሽፍጥ እንጅ ሀቅ አይጠበቅም ብለናል። በዚህ ሁኔታ ላይ ባለች አገር ውስጥ የሕዝብ መብት እንዲከበር በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ እየታገሉ ባሉት ወይም ጥያቄ ባቀረቡ ድርጅቶች ላይ እየደረሰ ያለው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፣ እስራት፣ አፈናና እንግልት እያወገዝን የትግል አጋርነታችንም ጭምር ለመግለጽ እንወዳለን። ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስቆጭና ተጠናክሮ መታገልን የሚጠይቅ ፈታኝ ወቅት ነው። በመሆኑም በአገራችን ውስጥ ያለውን አሳሳቢ ሁኔታ በመገንዘብ **<u>ኢህአፓን አንድ አድርጎና አጠናክሮ ትግሉን መቀጠል አማርጭ የሌለው ግዴታ ነው</u>** በሚለው መሪ ሃሳብ መሰረት ነው ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊና የኢሕአፓ እርምት እንቅስቃሴ ከአንድ ዓመት በላይ ውይይት ካደረጉ በኋላ የነበራቸዉን ልዩነቶች ዓርቀውና ተቻችለው **በአንድ ኢሕአፓ** ሥር ተሰባስበው ትግሉን ለማስቀጠል ስምምነት ላይ የደረሱት። ስምምነቱ ያተኮረባቸው ዋና ዋና ጥቦች፤

ሀ. በጥቂት ወራት ውስጥ አንድ ሁሉን አቀፍ የሆነ ጉባኤ ማዘጋጀት

ለ. ለጉባኤው ዝግጅት እንዲረዳ በየከተሞች የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም አብሮ መሥራት

ሐ. ኢህአፓን አንድ አድርጎና አጠናክሮ ትግሉን ለመቀጠል እንዲቻል በኢሕአፓ/ኢሕአሠና ኢሕአወሊ ትግል ውስጥ ያለፉ፣ ሆኖም ግን በተለያዩ መክንያቶች ራሳቸውን ከድርጅቱ አግልለውና አርቀው፣ የነበሩ የዛ ጀግና ትውልድ ጓዶች/ጓዲቶች በሙሉ የታሪኩ አካል በመሆናቸው በጥቂት ወራቶች ውስጥ ለምናደርገው ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ላይ በመሳተፍ አብረን የጀመርነውን ትግል አብረን ለመጨረስ ይቻል ዘንድ የሚቻለውን ያህል ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። እነዚህና ሌሎችንም በጎ ሀሳቦች በማጠቃለል የጋራ ስምምነት ላይ መድረሳችን ለአባሎቻችን፤ ለደጋፊዎቻችን፤ እንዲሁም አምባገነኑን የወያኔ ዘረኛ ቡድን ለሚታገሉ ድርጅቶች ሁሉ ሥናበስር በታላቅ ደስታ ነው።

ኢህአፓ ዴሞክራሲያዊና የኢህአፓ እርምት እንቅስቃሴ
አንድነት ኃይል ነው
ትግሉ ይቀጥላል

የጋራ ኮሚቴ
taskforce@gmail.com